# የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል የሚደረግበት ወቅት አሁን ነው!




**የመተንፈሻ አካላት ላይ በሽታ የሚያስከትል ቫይረስ የሚከሰትበት ወቅት ደርሷል!** ለከባድ ህመም የመጋለጥ ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ሰዎች እና የቤተሰቦቻቸው አባላት ቤት ውስጥ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማድረግ እንዳለባቸው ሊያስቡበት ይገባል። በርግጥ በመተንፈሻ አካል ቫይረስ የመያዝ እድሉን መቀነስ ለሚፈልግ ለማናቸውም ሰው የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማድረግ ትልቅ አማራጩ ነው።

## መጠቀም ያለብኝ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ምን አይነት ነው?

- N95/KN95/KF94 የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎች ከሁሉም የበለጠ ይከላከላሉ።
- የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎች ሲያደርጉ አፍንጫዎ፣ አፍዎ እና አገጭዎ ላይ ጠበቅ ማለት አለባቸው።
- ከ2 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማድረግ የሌለባቸው ሲሆን ማንም ሰው ሲተኛ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማድረግ የለበትም።

## Alameda County ከሚከተለው ውጪ የግዛቱን የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል አጠቃቀም መመርያ ይቀበላል፡

በአንዳንድ የጤና ክብካቤ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ከህሙማን ጋር ሲገናኙ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል እንዲጠቀሙ ይገደዳሉ።



## የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል መጠቀም የሚሰራው እንዴት ነው?

የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎች ተጠቃሚውን እና በዙርያው ያሉትን ሰዎች በCOVID-19 እና እንደ ፍሉ እና RSV በመሳሰሉ ሌሎች የመተንፈሻ አካል ቫየረሶች እንዳይያዙ እና ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳያስተላልፉት ይከላከሏቸዋል።



Public Health Department
Alameda County Health

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት:
[CDPH የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብ መደረግ ያለበት ጊዜ]